# እነግራዚያኒ

አንድ ትውልድ መትረው በጅምላ የፈጁ
የወጣት አበባ አፈር ውስጥ ያስረጁ
የምሁር አዝመራ አጭደው የወቁ
የሰውን ስብዕና በስየል የፋቁ
በፋሽስት ህዳሴ መግደል የተካኑ
ማህፀን አድርቀው ወላድ ያመከኑ
በግፍ አገዳደል የደም ጎርፍ አጉርፈው
ከናዚ ጭካኔ በልቅና ገዝፈው
በንጹህ ደም መስኖ ሞት ያለመለሙ
የሰው ደም ዋጅተው ቀይ የተቀለሙ
በራፍ ላይ ለጣሉት ተበሳስቶ አካሉ
ለሞተበት ጥይት ዋጋ ያስከፈሉ
በለቅሶ ዳስ ድንኳን ባዘን ቤት ዋይታ
ተነሽና ዝፈኝ ውረጅ ያሉ እስክስታ
የልጇ ገዳዮች የግፍ ግፍ እንዲሉ
ሀዘኗን በዘፈን ሥርዓ ያስመሰሉ
ደርግና ኢሠፓ ኮ/ል መንግሥቱ
ታሪክ በሚል ሽፋን "እኛና አብዮቱ"
የውሸት ገለባ ብሊጣ ነጎዴ
ቸርቻሪ ሆነዋል አትራፊ ነጋዴ።

አብርሃም በየነ